# ከኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ ኃይል

## ጋር በመተባበር በየሳምንቱ የሚታተም

# የመንግሥት እና የግል አጋርነት በኃይል ልማት ዘርፍ ያለው ሚና

ባለፈው ሳምንት ዕትማችን በአይነቱና በአግልግሎቱ ልዩ ስለሆነው የወላይታ ሶዶ ኮንቨርተር ስቴሽን የኦፕሬሽን፣ የክትትልና የጥገና ሥራን በተመለከተ የጣቢያው ዳይሬክተር ኢንጂነር ሀብታሙ ግርማ የሰጡንን መረጃ አጠናቅረን ማስነበባችን ይታወሳል።

በዛሬው ዝግጅታችን ደግሞ የኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ ኃይል በመንግሥት እና በግል አጋርነት ስለሚለሙ ፕሮጀክቶች ምንነትና ያሉበትን ደረጃ የተቋሙ የIPP & PPP ፕሮጀክቶች ቀረፃ መምሪያ ዳይሬክተር አቶ ተስፋዬ ጥላዬ የሰጡንን መረጃ እንደሚከተለው አቅርበንላችኋል።

የIPP እና PPP ፕሮጀክት ልማት ምነድነው? እንደ ተቋም መቼ ተጀመረ? ከሚለው ስንጀምር ፤ IPP ማለት በመንግሥት ስር ያልሆኑ የግል አልሚዎች (Independent power producers or non-utility generators) በኃይል ማመንጫዎች ላይ የሚሳተፉበት ማዕቀፍ ነው። የኃይል ማመንጫዎቹ ዲዛይንም ሆነ ፋይናንስ በግል አልሚዎች የሚከናወን ሲሆን ኃይል ካመነጩም በኋላ መንግሥታዊ ለሆኑ አገልግሎት ሰጪ ኩባንያዎች እና ለብሔራዊ የኃይል መቆጣጠሪያ ማዕከል እንዲሁም ለህብረተሰቡ /end user/ እስከ 20 ዓመት በሆነ የአማካይ ጊዜ ውስጥ የኤሌክትሪክ ኃይል የሚሸጥ የግል አልሚ መሆኑን ዳይሬክተሩ አብራርተዋል።

በተጨማሪም PPP (Public Private Partnership) ማለት የመንግሥት ተቋማት እና የግሉ ሴክተሮች በኃይል ማመንጫዎችና ማከፋፈያ ጣቢያዎች፣ እንዲሁም ማስተላለፊያ መስመሮች ላይ ከ20-25 ዓመት በሆነ የረጅም ጊዜ ውል በትብብር ወይም በአጋርነት የሚሠሩበት ማዕቀፍ ነው። ይህም የግል አልሚውን ስጋት ከመንግሥት ጋር በመጋራት በራሱ ዲዛይንና ፋይናንስ በማድረግ በሰጠው አገልግሎት ክፍያ የሚጠይቅበት አሠራር ነው። የመንግሥት እና የግል አጋርነት በሌሎች አገልግሎት መስጫ ማለትም በመንገድ፣ በቤቶች ልማት፣ በጤና ወዘተ ዘርፎች ላይ ትኩረት አድርገው ሊሰሩ የሚችሉ መሆኑን ገልፀዋል።

አቶ ተስፋዬ እንደገለፁት፤ የግል አልሚዎች የፋይናንስ አቅማቸውን ተጠቅመው በኃይል መሠረተ ልማት ላይ መዋዕለ ንዋያቸውን እዲያፈሱና እንዲያስተዳድሩ ማድረግ የIPP/PPP ፕሮጀክት ልማት ማዕቀፍ ዋነኛ ተልዕኮ ነው። ይህን መሰል የትብብር ማዕቀፍ ለሀገር ልማት በርካታ ጠቀሜታዎች እንዲኖሩት ያደርጋል። በተለይም ፕሮጀክቶቹ ሲጠናቀቁ የግሉ ዘርፍ ኃይል የማመንጨት ሥራውን ለረጅም ዓመት ይዞ ስለሚቀጥል ሙሉ ወጪውን እንዲሸፍን ያስችለዋል።

በተጨማሪም የግሉ ዘርፍ የፈጠራ አቅሙን ተጠቅሞ በኃይል መሠረተ ልማት ዲዛይን እና አገልግሎት አሰጣጥ ላይ የተሻለ ውጤት እንዲያመጣ ያግዘዋል። እንዲሁም የፕሮጀክቶችን መጓተትና ተጨማሪ የግንባታ ወጪዎችን በእጀጉ ይቀንሳል ወይም ያስቀራል። የአገልግሎት አሰጣጥን ጥራት በመጨመር፣ ለአገር በቀል ተቋማትም የዕውቀት ሽግግርን በማስፋት፣ ተፈጥሯዊ ሀብትን በአግባቡ ለመጠቀም የሚያሻሽል ነው። ይህም የIPP/PPP ፕሮጀክት ልማት ምን ያህል ለተቋምም ሆነ ለአገራዊ ልማት መፋጠን ፋይዳው የጎላ ስለመሆኑ ማሳያዎቹ ናቸው ብለዋል።

የIPP & PPP ፕሮጀክት አተገባበር እንደተቋም በታቀደው መልኩ ባይሆንም ከጊዜ ወደጊዜ አበረታች ሂደት ያሉት መሆኑን ያወሱት ዳይሬክተሩ፤ በማዕቀፉ የሚተገበሩ ፕሮጀክቶች የረጅም ጊዜ ውል የሚገባባቸው እና ውስብስብ ባህሪ ያላቸው ናቸው። በተለይም ከፕሮጀክት ልየታና መረጣ ጀምሮ የቅድመ አዋጭነት ጥናት፣ ዝርዝር የአዋጭነት ጥናት፣ ፋይናንስ የማፈላለግና የግዥ ሂደት፣ የግንባታ ሥራዎች ረጅም ጊዜያትን የሚወስዱና ከፍተኛ ወጪን የሚጠይቁ ናቸው። እንዲሁም ከግንባታው በኋላም የግል አልሚው ከ20-25 ለሚደርሱ ዓመታት አገልግሎት የመስጠት ውል የሚገባ በመሆኑና በእነዚህ ዓመታት ውስጥ ሊፈጠሩ የሚችሉ ስጋቶችን ለመገመትና ለመተንተን ከፍተኛ ጥንቃቄ የሚፈልግ ውስብስብ የሥራዎች ያሉበት ነው።

አቶ ተስፋዬ እንደሚናገሩት፤ የግል አልሚዎች በዘርፉ ላይ መዋዕለ ነዋያቸውን ለማፍሰስ በዓለም አቀፍ የፋይናንስ አበዳሪ ተቋማትና ኢንቨስተሮች ተቀባይነት ያለው ትርፋማ /Bankable/ ፕሮጀክት ይፈልጋሉ። አዋጭ ፕሮጀክትን እያሠራ ያለው መንግሥት ወይም ተቋም ደግሞ በውጭ ምንዛሬ የፋይናንስ አቅሙ /credit worthiness/ አስተማማኝ መሆን አለበት። እንዲሁም የግል አልሚዎች ወደ ውጭ ሀገር የውጭ ምንዛሬ ማስተላለፍ እንዲችሉ ተቀማጭ የገንዘብ ድጋፍ ወይም ፈሰስ /Liquidit support/ ይጠይቃሉ። እነዚህና መሰል ችግሮች ደግሞ በIPP/PPP አሠራር መሰረት እንዲፈፀሙ የሚታሰቡ ፕሮጀክቶችን ወደ መሬት ለማውረድ ፈታኝ አድርገውታል።

ይሁንና መንግሥት ለዘርፉ ከፍተኛ ትኩረት በመስጠቱ የተለያዩ የሕግ ማሻሻያዎች፣ ፖሊሲዎች መመሪያዎች እንዲሁም በ2010 ዓ.ም የወጣውን የመንግሥትና የግል አጋርነት አዋጅ ጨምሮ ሌሎች አስቻይ ሁኔታዎች /enabling environment/ ተዘጋጅተዋል። በተለይም በፋይናንስ በኩል ያለውን ተግዳሮትም ለመቅረፍ ተቋሙ ከገንዘብ ሚኒስቴር ጋር በመሆን የውጭ ምንዛሬ ዋስትና በኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ እንዲሰጥ እየሠራ ይገኛል።

ከፋይናንስ እና ግብዓት ዝግጅት በተጨማሪ አልሚዎችን በአግባቡ ሊያስተናግድ የሚያስችል አደረጃጀትና ኃይል መቀበያ አስተማማኝ የኃይል ቋት ሥራዎችን ማከናወን ከፍተኛ ትኩረት የሚፈልግ ጉዳይ ነው። በመሆኑም እንደተቋም ዘርፉን የሚመራ የIPP & PPP ፕሮጀክቶች ቀረፃ መምሪያ እንዲደራጅ ተደርጓል። መምሪያው በዋናነት በመንግሥትና በግል አጋርነት የሚገነቡ ፕሮጀክቶችን ከገንዘብ ሚኒስቴር ጋር በመሆን የማስፈጸም ኃላፊነት ያለው ነው። በተጨማሪም የተጠኑ ፕሮጀክቶችን እያቀረበ በቦርድ እንዲጸድቁ ማድረግ፤ በትብብር ለሚሠሩ ፕሮጀክቶች ከአማካሪ ድርጅቶች ጋር በመሆን የባንክ ሰነዶችን ማዘጋጀት፤ ጨረታዎችን ማካሄድ፣ ፕሮጀክቶችን መግዛት፣ ከተገዙም በኋላ የማስፈጸም ኃላፊነትን ማውጣት ለመምሪያ የተሰጡ ተልዕኮዎች ናቸው።

የIPP & PPP ፕሮጀክቶች ቀረፃ መምሪያ እንደተቋም በአዲስ ከተደራጀ ወዲህ ከገንዘብ ሚኒስቴር ጋር በመሆን የተለያዩ ሥራዎችን እየሠራ እንደሚገኝ የጠቆሙት አቶ ተስፋዬ በዘርፉ የሚስተዋሉ ችግሮችን መቅረፍ ከተቻለ በቅርብ ጊዜያት የIPP /PPP አተገባበር ውጤት ሊያስገኝ እንደሚችል ግምታቸውን አስቀምጠዋል።

የኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ ኃይል

በብርሃንና ሰላም ማተሚያ ድርጅት ታተመ